# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 1 ቁጥር 4 መጋቢት ፩ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም.


## <u>የኢትዮጵያ ሴቶች፤ የትግል እመቤቶች</u>

*(ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን 103ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሴቶች በፆታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን በደል አድልዎና ጭቆና ለመላቀቅ፣ ለማስወገድ ከአደረጉት ትግል ጋር በመያያዝ የሚታሰብ፣ የሚከበር ዓለም አቀፋዊ በዓል ነው። እ.አ.አ በ1911 መከበር የጀመረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 (የካቲት 29 ቀን, 2006 ዓ.ም.) እነሆ 103 ዓመቱ። ዕለቱ ዓለም በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መድረኳ ሴቶችን እኩል ታሳትፍ ዘንድ፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ መድሎዎች ይወገዱ ዘንድ መከበር የጀመረው ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናከብር ሀገራችን የሴቶችን ጥያቄ መልሳለችን? የሚለውን እንድንዳስስ ግድ ይለናል። በሀገራችን ኢትዮጵያ የሴቶች ተሳትፎን መቃኘት፣ ሴቶች ከፆታ ጥያቄ ባሻገር ለመሰረታዊ የፖለቲካ ጥያቄ ያበረከቱት አስተዋጽዎና የከፈሉት መስዋእትነት ሊዳሰስ ይገባዋል።

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕለቱ በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል። ያለፈውን ዘመን ተጋድሎ ዘክረው ለአሁኑና ለቀጣዩ ትውልድ ትምህርት ጥለው ከሚያልፉ በዓላት አንዱ ነው። በዓለም ሕዝቦች በተለይም በሴቶች መብት ተቆርቋሪዎችና ደጋፊዎች ዘንድ ከዛሬ 103 ዓመት ጀምሮ ማርች 8 ሲከበር ኖሯል።

ዓለም አቀፉ የሴቶች ቀን በየዓመቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን አግኝቶ ለመከበሩ ትልቁን ሚና የተጫወቱት በዘመኑ የሴቶች የበታችነት እጅግ ያስቆጫቸውና ለውጥ ለማምጣት በተነሱ ጥቂት ሴቶች አማካይነት ነው። ለዚህም ክላራ ዜትኪን ተጠቃሽ ናት። ክላራ በአገሯ ጀርመን የነበረው ሶሻሊስት ፓርቲ ሴቶችን የማይወክል ብሎም ለሴቶች መብትና ደህንነት መከበር ፊቱን ያዞረ ስለነበር ይህንን ሥርዓት ለመታገል የተነሳች የቁርጥ ቀን ልጅ ነበረች። ይህ ጥረቷ ደግሞ ከብዙ ድካም በኋላ ፍሬ ሲያፈራ ተከታይ አላጣችም።




ክላራ በአገሯ ጀርመን የመጀመሪያውን ንቅናቄ ካካሄደች በኋላም በኮፐን ሀገን ላይ ሁለተኛውን የሴቶችን መብት የተመለከተ ኮንፈረንስ አካሄደች። በኮንፈረሱም ከ17 የዓለም አገራት የተውጣጡ አንድ መቶ ያህል ሴቶች ተሳታፊ ነበሩ። ይህም ለክላራ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሴቶችም አቅም ሆኖላቸው የዓለም መንግሥታትም ለጉዳዩ ትኩረት ይሰጡት ጀመር።

በእዚህም የተነሳ ማርች 18 ቀን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሆኖ እንዲታሰብ እ.አ.አ በ1911 ተወሰነ። በአውስትራሊያ፣ በዴንማርክ፣ በጀርመን እንዲሁም ሲውዘርላንድ ያሉ መንግሥታትና ሴቶችም ዕለቱን በታላቅ ደስታ በመቀበል ያከብሩት ነበር። በኋላም በተለያዩ ምክንያቶች ዕለቱ ማርች 18 መከበሩ ቀርቶ እ.አ.አ 1913 ወደ ማርች 8 ቀን እንዲሆን ተወሰነ፤ ይህ ዕለትም እስከ አሁን ድረስ በመላው ዓለም እየተከበረና እየታወሰ ይገኛል።

ወደ ኢትዮጵያችን ስንመጣ፤ የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ ያላት ሀገራችን ስንል መነሻችን በሀገራችን የመጀመሪዋ ገዢ፣ ንግሥት ሴት እንደነበረች የታሪክ መዛግብት ወደ ንግሥተ ሳባ ይወስዱናል። ይህ በፖለቲካው መስክ የሀገራችን ሴቶች የነበራቸውን ተሳትፎ ቢያንጸባርቅም ሀገራችን ሴቶች በሴትነታቸው የሚደርስባቸውን በደል ቀርፋለች ማለት አይደለም። የቅርቧም ንግስት ዘውዲቱና ሀገራችንን ሊጎዳና ሊወር የመጣውን ጠላት ሁሉ ለመቋቋም በተደረጉ ትግሎች የሴቶች ተሳትፎ ቀላል ባይሆንም ወራሪ ፋሽስትን በማንበርከክ ስሟ ከፍ ያለው ጀግናዋ ጣይቱ ብጡል ሴቶች የፆታ የበታችነት ሳይበግራቸው በከፍተኛ እርከን ላይም አመራር በመስጠት ያስመዘገቡትን አኩሪ ተግባር አንጸባራቂ ነው።

በዐድዋ ጦርነት ለኢትዮጵያውያን ድል መቀዳጀት የእቴጌ ጣይቱ መቀሌ የመሸገውን የኢጣልያን ጦር የፈቱበት ዘዴ ብልህነታቸውንና የአመራር ብቃታቸውን መስካሪ ነው። የጣይቱን ዘዴ ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ "ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ" በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ይገልጹታል


LA REGINA TAITU.

". . . ንግሥቲቱም እቴጌ ጣይቱ ከድንኳን ብቅ ብለው ግምጃውን አጥር አስገልጠው ሲመለከቱ አዛዥ ሚካኤል አጠገባቸው ቁሞ ነበርና ወደሱ ዓይናቸውን ዞር አድርገው ተናገሩ። አንተ ሂድና ውሃውን ለመያዝ ይመች እንደሆነ ስፍራውን ሰልለው። ሊቀመኳስ አባተም ሥፍራው ጎድጓዳ ነው፤ ለኢጣሊያኖችም ቅርባቸው ነው። የውሃውና የምሽጉ ርቀት 150 ክንድ ይሆናል። ነገር ግን እኔ በመድፍ በሩን እጠብቀዋለሁ። ዘበኛውም ለዓይን ሲነሳ ገብቶ ከወንዙ ይተኛል ብሎ ላከ። ይህም ነገር በእቴጌ ዘንድ የተወደደ ሆነ። ለንጉሠ ነገሥቱም አመለከቱ። አጤ ምኒልክም እሺ እንዳልሽ አሉዋቸው።"

በዚህ ዘዴ መቀሌ የመሸገውን ፋሽስት ወራሪ በውሃ ጥም ቀጥተው ከምሽጉ እንዲወጣ በማድረግ ኢትዮጵያውያንን ለድል ያበቁ እቴጌ ጣይቱ በሴትነታቸው የጀግና እመቤት፣ የሀገር ኩራትነታቸው በአሁኑም ትውልድ "ጣይቱ እመቤቲቱ" አዘምሮላቸዋል።

"በአምስቱ ዓመት የፋሽስት ኢጣልያን ወረራ ወቅት ፋኖዎቹ ከጠላት መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ነበራቸው። ወደ ጠላት ጦር ጠጋ ብለው የሚያደፍጡ ቃፊሮች የጠላትን ጦር እንቅስቃሴ ይዘግቡላቸው ነበር። ከሁሉም በላይ መረጃ በመሰብሰብ በኩል ቁልፍ ሚና የተጫወቱት ግን የውስጥ አርበኞች ነበሩ። ከጠላት ጋር አብረው እየኖሩ የጠላትን ጦር ጥንካሬ፤ የታለሙ ዘመቻዎችንም ሆነ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ አርበኞቹን አስቀድመው በማስጠንቀቅ የጠላትን ዕቅድ ያጨናግፉ ነበር።...




ለዚህም ሁሉ ሥራ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ስለማይጠረጠሩ በተለይ ያመቹ ነበሩ። ከሴቶች የውስጥ አርበኞችም ከፍተኛ ዝና ያገኘችው አርበኞች አዲስዓለም የመሸገውን የጠላት ጦር እንዲደመስሡ ሁኔታዎችን ያመቻቸችላቸው ሸዋረገድ ገድሌ ናት።" የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966፤ ባህሩ ዘውዴ፤ 1989 አዲስ አበባ።

ሸዋረገድ ገድሌና መሰል የአርበኛ እመቤቶች ትውልድ ሊያስታውሳቸው ይገባል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናስታውስ በሀገራችን ኢትዮጵያ በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን አስከፊ ጭቆናና በደል በማሰብ ነው። ያለ ዕድሜ ጋብቻ በሚደርስባቸው ስቃይ፣ አስገድዶ መድፈር፣ መጥለፍ፣ አካሏን ማበላሸት፣ ከአቅም በላይ ለሆነ የጉልበት ሥራ መዳረጋቸው፣ በዝሙት አዳሪነት አካልን በመሸጥ የሚደርስባቸውን እንግልትና በሽታ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በመካከለኛው ምሥራቅ በተለይ በአረቡ ዓለም እየደረሰባቸው ያለውን የመረረ እንግልትና መከራ በማስታወስ ነው።

በ1966 ዓ.ም ሕዝባዊ አመጽ ይዞ ከተነሳው ጥያቄ አንዱ የሴቶችን መብት የተመለከተ ነበር። ለዚህም ከውጭ ሀገር ተምረው ወደ ሀገር በተመለሱና ሀገር ውስጥ ትግሉን በግንባር ቀደምትነት በሚመሩት ሴት ታጋዮች አማካይነት የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ ተመሰረተ። ከሴቶች ትምህርት ቤት፣ ከፋብሪካና የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሴራተኞችን ጨምሮ ወደ 300 የሚጠጉ ሴቶችን ያካተተ ሴሚናር ለአንድ ሳምንት በፓርላማ ውስጥ አካሄዱ። እነዚሁ ሴቶች ነበሩ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በማርች 8 እንዲከበር በአደረጉት ጥረት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1968 ዓ.ም. በሀገራችን በታላቅ ድምቀት ተከብሮና የብዙሃኑንም ጥያቄ ይዞ እንዲሰለፍ ግምባር ቀደምትነት ሚና የተጫወቱት።

በወቅቱ የነበረዉ የደርግ አገዛዝ የሴቶችን ጥያቄ ለስልጣን ማራዘሚያዉ እንጂ በሴቶች እኩልነት አምኖ የሴቶችን ጥያቄ ለመመለስና ሴቶችን በእኩልነት ለማስተዳደር ስላልሆነ እረብሻ አስነሳቻሁ በማለት የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴን ቢሮ ዘግቶ ድርጅቱን አፈረሰዉ። ደርግ በሴቶች ጥያቄ ሽፋን የራሱን መፈክር የሚያስተጋቡ አድርባይ ሴቶችን በማሰባሰብ የሴቶችን ትግል ለአምባገነኖች የስልጣን ማጠናከሪያ አድርገዉታል። ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በመሰረቱ ሲመሰረት ሴቶች የህብረተሰቡን የፖለቲካዊዉንና ኢኮኖሚያዊ ጭቆናን በመታገል ለኩል ስራ እኩል ክፍያ እንዲደረግላቸዉ፣ በወሊድ ጊዜ በቂ እረፍት እንዲሰጣቸዉና ሌሎችም በሴትነታቸዉ ምክንያት የሚደርስባቸዉን ጭቆናና በትግላቸዉ የተገኙ ድሎቻቸዉንም የሚያስታዉሱበት የራሳቸዉ ቀን ነዉ። ቢሆንም ከወንድ ትምክህተኝነት የተላቀቁና የሴቶችንም ጥያቄ ከሌሎች ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ጋር የሚያያይዙ ወገኖችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ይህንን ቀን በማክበር ማስተማሪያ ያደርጉታል።

በየካቲት 1966 አብዮት ወቅት ኢሕአፓም ሴቶች የትግሉ ግማሽ ኃይል መሆናቸውን በመገንዘብ፤ ለተቋቋመው የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ ድጋፉን በመስጠት የሴቶችን የመብት ትግል እራሳቸው ይመሩ ዘንድ የተደረገው ጥረት አኩሪ ውጤትን አስመዝግቦ ለኢትዮጵያ ሴቶች ትግላዊ ድርጅት (ኢሴትድ)ና ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣቶች ሊግ (ኢሕአወሊ) ምሥረታ መሰረቱን የጣለው በሴቶች እህቶቻችን የአመራር ብቃት እንደነበር የሚካድ አይደለም።

የሴቶች ጥያቄ እራሱን የቻለ ግን መላ ኅብረተሰቡንም የሚመለከት በመሆኑ፤ ጥያቄው ምላሽ ሊያገኝ የሚችለው ከዴሞክራሲያ መብት መከበርና ከፖለቲካ ሥልጣን አኳያ መሆኑን በመረዳት የያ ትውልድ ጀግኖች፣ የትግል እመቤቶች፣ አስመዝግበው ያለፉት የነፃነት ተጋድሎ፣ የሀገር ፍቅርና የሕዝብ አለኝታነት፣ አስተማሪነቱ የጎላ ነውና ሊዘከርና ሊከበር የሚገባው በመሆኑ አልዘነጋናችሁም።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. ግብታዊ እንቅስቃሴ በመላ ሀገሪቷ ከመከሰቱ በፊት በዓፄ ኃ/ሥላሴ አገዛዝ በተለያየ ወቅት በርካታ ተቃውሞዎች ገጥመዋቸዋል። በተለይ ከ1953 የታህሳስ ንቅናቄ በዋላ ፊውዳላዊው አገዛዝ የተረጋጋ ዘመን አልነበረውም። የተማሪዎችና የወቅቱ ተራማጅ ኃይሎች በተናጠልና በቡድናዊ መልክ በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለዓለም ለማሳወቅ የተለያዩ ሙከራዎችን አካሂደዋል። በድርጊቱ ቀዳሚው የተሳካ ሆኖ ቀጣዩ ቢከሽፍም መልዕክቱ ግና በተለያዩ የዓለም ሚዲያዎች የአየር ሽፋንን አግኝቷል። የ1962 ዓ.ም. እና የ 1965 ዓ.ም. የአይሮፕላን ጠለፋ።


ማርታ መብራቱ
Marta Mebrahtu

ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመር ቁጥር 730 ቦይንግ ጄት አይሮፕላን 94 መንገደኞችና 9 የአይሮፕላኑ ሠራተኞች አሳፍሮ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል በአሥመራ በኩል ወደ አቴንስ ሮምና ፓሪስ ለመብረር ከአዲስ አበባ ተነስቶ 13 ደቂቃ ያህል እንደበረረ በሰባት ታጋዮች መጠለፉ ይታወቃል። የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርስቲ የሕክምናን ኮሌጅ ተማሪ ማርታ መብራቱ ከጠላፊዎቹ አንዷ በመሆን ሕይወቷን በመሰዋት በፊውዳሉ አገዛዝ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ ለዓለም ያሳወቀች ቀዳማይ የትግል እመቤት ነበረች።

በየካቲት አብዮት ወቅትና ከዚያም በኋላ ሴቶች ግንባር ቀደም ሆነው አረመኔውን የደርግ አገዛዝ ታግለዋል። የትግል ጓዳ እናቶች የከተማው ትግል አስተዋጽዎ አስደናቂ ነበር። ሴቶች በትግሉ አስከፊውን የፋሽስቶች ዱላና መከራ አስተናግደዋል። ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ የደርግ ገራፊዎችና ገዳዮች ስሜት ማርኪያ በመሆን የስነልቦናዊና የአካል ጥቃት ሰለባ ሆነዋል። እስከወዲያኛው በፋሽስት አውሬዎች ተበልተዋል። በጨካኝ ፋሺስቶች በትር የተዘረረችው የዘጠኝ ወር ነፍሰ ጡሯ ዳሮ ነጋሽ ልጆችሽ አለን፤ ዐመጽ ያጋተው ጡትሽ አልነጠፈም ! እንላታለን። ትግል ሕይወቴ ብላችሁ ለሀገርና ለህዝብ ላይ ታች እንዳላችሁ በግፈኞች እጅ ወድቃችሁ፤ አካላችሁ ተተልትሎ በስቃይ ያንቀላፋችሁ  የያ ትውልድ አባላት ታሪክ ሰርተው ካንቀላፉ እህቶቻችን ማዕከል ናችሁ።

በዱር በገደሉ በአሲምባ ተራራ ፋኖ ተሰማራ ብላችሁ ከወንድ ወንድሞቻችሁ በበለጠ ሁኔታ፤ መብታችሁ ተከብሮ፣ ሚናችሁ ታውቆ፣ ጀግንነታችሁ ተደንቆ፤ ትግሉን የመራችሁ፤ በደማችሁ አሲምባን ያደመቃችሁ፣ ኢትዮጵያዊነትን የፃፋችሁ ድላይና መሰል እህቶቻችን፣ ከሴቶችም አልፎ ለህዝብ መብትና ለሀገር አንድነት የተዋደቃችሁ ክብር ለናንተ ብለናል።




"…ድላይ የብዙኃን ኢትዮጵያዉያን ራዕይ ነች። መካሪ እህት አይዞን ባይ ጓዲት፣ ቆፍጣና ተጋዳይ፣ መረር ያለች የዕውነት ወታደር። ተርባ የደከሙት ይብሉ ብባለች፣ ተጠምታ የተጠሙት ይጠጡ ብላለች። በአጠጋቢ የተሰለፉት ወንድሞቿና እህቶቿ ሩህሩህ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጓዲት፤ ለኢትዮጵያ ደግሞ ከወደቁት ብርቅዬና ትክ የለሽ ጀግና ልጆቿ አንዷ ድላይ። እንደ ስሟ ባለጥልቅ ትርጉም ድላይ - ፍላጎት (የነፃነት ፍላጎት) ድላይ - የድል ሴት።" ድላይ ከሚለው ጽሁፍ፤ ቴዎድሮስ ቺኪ

"በስልክ ተደውሎ የአሲምባ ፍቅር የሚል መጽሃፍ ፈልጊና አንብቢ የእህትሽን ታሪክ የያዘ መጽሃፍ ነው ስባል ልክ በህይወት መጣችልሽ የተባልኩ መሰለኝ ሲቃ እያነቀኝ ወደ መጻህፍት ቤት ገሰገስኩ ስደርስም ለመጠየቅ አቃተኝ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ ከንፈሬ ሁሉ እየተርበተበተ መጽሃፍ ሻጪን ጠየቅኋት አለ ስትለኝ ልስማት አልኩና ደነገጥኩ እንደገና ከዚያም እራሴን ተቆጣጥሬ መጽሀፉን ተቀብየ ሳም አደረግሁት ሴትዮዋ በመገረም አየችኝ። ደፍሬ ግን ለማንበብ አልችል አልኩኝ ደስታ ይሁን ሀዘን አላወቅሁም ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ተሰማኝ ከዚያም ለ4 ቀናት ያክል አመመኝ እና ተኛሁ እንደድርሳነ ሚካኤል አቅፌው ተኛሁ ከዚያም እራሴን አረጋግቼ ማንበብ ጀመርኩ::

ምንም እንኳ የምትወዳቸውን ጓደኞችህን እና ያሳለፍከውን የውጣ ውረድ ዘመን እያሰብክ ሰላም ባይሰማህም ለእናትና አባትህ እንኳን እግዚአብሔር አተረፈላቸው ከነሱም አልፎ ለእኔና እኔን መሰል ያለ ታሪክ የቀሩ ቤተሰቦች ላሏቸው ሲል አምላክ እንኳን ከዚህ ቀን አደረሰህ። እህቴ መሞቷ ብቻ ሳይሆን የታሪክ ተካፋይ ባለመሆኗ አእምሮዬ ቆስሎ ይኖር ነበር።

በአፈ ታሪክ ታጋዮች ሁሉ ጀግንነቷን ያላትን ጥሩ ስነምግባር ይተርኩልኛል ነገር ግን የታሪክ መዝገብ ላይ አላሰፈሯትም። ከከተማ ሳይወጡ በቀይ ሽብር የተረሸኑት ደርግ እንደተደመሰሰ በቤተክርስቲያን መቃብር ቤት ተገንብቶ ከተረሸኑበት አጽማቸው ወጥቶ በክብር እንደገና ተቀበሩ እናም የቀይ ሽብሮች መቃብር ቤት ሲታይ ቤተሰቦቻቸው አልቅሰውም ሆነ ስቀው የልጆቻቸውን ታሪክ ያወሳሉ። ሌሎች ደግሞ በበረሃ የተሰውት ደግሞ የሰማእታት ሃውልት ተብሎ በተገነባው ውስጥ የአንድ ታጋይ ስሙና ትውልዱ የሰራው ታሪክ የተሰዋበት ቦታ ሁሉ በዝርዝር ይገኛል። የእኔ እህት ግን ውሻ ስታባርር የሞተች ይመስል የታሪክ መዝገብ ላይ ስሟ የለም አንዳንድ ታጋዮችን ሳነጋግራቸው እሷ የተሰዋችው ብአዴን ሳይመሰረት በኢህአፓ ዘመን ነው ይሉኛል ኢህአፓ የውጭ ዜጋ ይመስል። እናም አእምሮዬ ሲደማ የቆየበት ታሪክ ዙሮ በአሜሪካ ሲመጣ ከቁስሌ ተፈወስኩ።" ድርብ ምናለ፤ የድላይ እህት

“መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ አረመኔው ግርማ ከበደ ከአጃቢዎቹ ጋር ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሰተት ብሎ ገብቶ ሠራተኞቹን ለስብሰባ እንደሚፈልግ ተናገረ። ...ከተሰበሰበው ሰራተኛ መሀል የስም ዝርዝሩን እያነበበ አስወጣ። ዘጠኝ ብቻ ተገኙ።

ዳሮ ነጋሽ ከዘጠኙ መሀል አንዷ ብትሆንም ስብሰባው ላይ አልነበረችም። እስር ቤት ለሚገኘው ባሏ ስንቅ አቀብላ አርፍዳ ስትመጣ የውጭ በር ላይ ጠብቀው ነው የያዟት።...


ዳሮ ነጋሽ
Daro Negash

መጋቢት 15 ቀን 1969ም ዓ.ም. አዲስ ዘመን ጋዜጣ “...በማተሚያ ቤቱ ሐቀኛ ተራማጆችና በቀበሌ 07 ታጋይ ጓዶች የተጋለጡት ቀንደኛ ፀረ አብዮተኞች በቁጥጥር ሥር ውለዋል።” የሚለውን ዜና ይዞ ወጣ።

ጋዜጣው ይህንን ዜና ይዞ በወጣበት ዕለት ዘጠኙ ሠራተኞች ቀድመው ተረሽነው፤ ሬሳቸው ሜዳ ላይ ተዘርግቶ፤ ህዝቡን ዕንባ እያራጨ ነበር።...ከዳሮ ጋር ሴቶች ሦስት ሲሆኑ ወንዶች ስድስት ናቸው። የአንድ ሴት ጡትና የአንድ ወንድ ብልት ተቆርጦ ወድቋል። መልካቸው እንዳይታወቅ ዓይናቸው ጠፍቷል፤ ፊታቸው ተጨፍጭፏል።...

የዳሮ ነጋሽ ሬሳ በህዝቡ ግፊት ወደ ሀኪም ቤት ተወሰደ። ሽል እንደያዘች አትቀበርም። ወደዚህ ዓለም ለመምጣት ጥቂት ቀናት የቀሩት ህፃን በሕይወት መኖር ያለመኖሩ መታወቅ አለበት። ምናልባት ለጉድ ቢተርፍስ?. . . ሕፃኑ ትንፋሹን ይዞ ከማህፀኗ ውስጥ ብቅ አለ። የእንግድነት ድምፁንም አሰማ። ይሁን እንጂ ብዙ አልቆየም። በመከራ ይዞአት የመጣው የሲቃ ነፍስ ወዲያው ጭልጭል ብላ ጠፋች።” ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፤ ቅጽ አራት፤ 1991 አዲስ አበባ።

ማርች 8 ዓለም አቀፍ ሴቶች ቀንን ስናስታውስ ከፆታ ጭቆና አልፋ ለሀገራችን ሕዝብ የዴሞክራሲ መብት መከበር ድምጿን ባሰማች የተረሸነችዋ የዘጠኝ ወር ነፍሰጡሯ ዳሮ ነጋሽ ከጎሊና የማትጠፋ የፋሽስቶችን የጭካኔ ደረጃ መስካሪ ታሪካችን ናትና ዘክረናታል።


ከ15ቀ30 ሶፍያ አየለ ገ/መስቀል Sofia Ayele G/Meskel

“5.10 “ትወገድ”

ሶፊያ አየለ ገብረመስቀል ዕድሜዋ 22 ዓመት፤ ሥራዋ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ አድራሻዋ አዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 30 ነበር። ሶፊያ በ1968 መጨረሻ ላይ ለ”ሕገወጡ” የኢሕአፓ ቡድን ተመልምላለች ተብሎ በየካቲት ወር 1970 ተይዛ ታሠረች። በደርጉ ምርመራ ክፍል በሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የተፈረመ መግለጫ ለቋሚ ኮሚቴ የሀገርና የሕዝብ ደህንነት ጉዳይ ኃላፊዎች “አደገኛ ፀረ-አብዮተኛ ስለሆነች የማያዳግም እርምጃ ሊወሰድባት ይገባል” ከሚል አስተያየት ጋር ግንቦት 1 ቀን 1970 ቀረበ።

በምርመራ መግለጫው የውሣኔው አምድ ስር የሚከተለው በደረጃ ታዘዘ።

ኮለኔል ካሣሁን ታፈሰ፤

> ፍፁም የለየላት ቀንደኛ ፀረ-አብዮተኛ ስለሆነች አብዮታዊ ቅጣት ይገባታል። ለውሳኔ ለዋና ፀሐፊ ይቅረብ። 4.9.70

ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ፤

> ሕዝብ ደህንነት ባቀረበው መሠረት ትወገድ።4.9.70

ኮለኔል ካሣሁን ታፈሰ

> ጓድ ሻለቃ ብርሃኑ፤ በዚሁ መሠረት ይፈፀም።4.9.70

ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ፤

> በውሳኔው መሠረት እንዲፈፀም ይሁን።4.9.70"

በወንጀል የተቀጡ ሰዎች መመዝገቢያ ካርድ ላይ "በወንጀል መዝገብ ቁጥር ሰ-111 በ4/9/70 በሞት ተቀጣች" ተብሎ ተመዘገበ።" ደም ያዘለ ዶሴ፤ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፤ ጥር 2002 አዲስ አበባ።

በደርግ አገዛዝ ፊርማም ጥይት ነበር። ሶፍያ አየለና መሰል የያ ትውልድ ሴቶች ለተነሳችሁበት ዓላማ ጽናትና በቆራጥነት በከፈላችሁት መስዋዕትነት ቆመን እንድንሄድ አድርጋችኋል፣ ሕይወት ዘርታችሁብናልና ምስክርነታችን ይድረሳችሁ።

«ያ ትውልድ ተቋም» ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን (ማርች 8) ስናከብር፤ ሴቶች ማኅበራዊ ሕይወትን ጨምሮ ለመብትና ለነፃነት በተደረገው ተጋድሎ ያስመዘገቡት ታሪክና የተጫወቱት ሚና በሚገባ የተዘገበ አለመሆኑ ከአሁኑ ትውልድ ጋር የታሪክ ክፍተት ፈጥሯል እንላለን። «ያ ትውልድ ተቋም» የኢትዮጵያ ሴቶችን የትግል ታሪክ በማሰባሰብ የአሁኑና መጪው ትውልድ ይመራመርበት፣ ያጠናበት፣ ይጽፍበት፣ ይማርበት ዘንድ የሚደረገው ጥረት የሁሉንም ትብብር ጠያቂ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስገንዘብ እንወዳለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናከብር፤ በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም በሴቶች ላይ የሚደርሰው ግፍና መከራ ያበቃ ዘንድ በመመኘት ነው። ያልፍልናል ብላችሁ፤ ሳትወዱ ለስደት ተዳርጋችሁ በየበረሃውና በየዱሩ የምትንገላቱ ወገኖቻችን ስቃይና ሰቆቃ እየተሰማን በተለይ በአረቡ ዓለም እየደረሰባችሁ ያለው መከራ፣ ስቃይና እንግልት አብቅቶ እምዬ ኢትዮጵያ ሁላችንንም ከያለንበት የምትሰበስበን ቀን ይቀርብ ዘንድ በመመኘት ነው።

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 ታሪካችን ነው!

ለዕቅድ ስኬታማነት የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው!!!

**ያ ትውልድ ተቋም**
**ድረ ገጽ ፡** www.yatewlid.org, www.yatewlid.com
**ኢሜል ፡** yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com